የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት

የፍትሀብሄር ክፍል

የአነስተኛ ክሶች እና የእርቅ ቅርንጫፍ

BuildingB, 510 4th Street N.W., Room120Washington, D.C.

20001ስልክ(202)879-1120


# ደሞዝ በአደራነት እንዳይያዝና ነጻ እንዲሆን ለባለ ገንዘብ የተዘጋጀ ማስታወቅያ

Notice to Debtor of Non-Wage Garnishment and Exemptions

## ገንዘብዎ፣ ሒሳቦችዎ ወይም ገቢዎ በፍርድ ያሸነፈውን ለመክፈል ሊወሰዱ ይችላሉ። እባክዎን ይህንን ማስታወቅያ ተጠንቅቀው ያንብቡ።

**እርስዎ ተከሳሽ ከሆኑና፣ በጉዳይዎ ላይ የሚያያይዝ ትእዛዝ (Writ ofAttachment) ከተላለፈብዎ፣ ይህንን ማስታወቅያ አንብበው ለመብትዎ መከላከል ይኖርብዎታል።** የሚያያይዝትእዛዝ (WritofAttachment) አንድ ፍርድ ቤት ውስጥ የክስ ጉዳዩን ያሸነፈ ሰው ገንዘብ ለመሰብሰብ የሚጠቀምበት ሕጋዊ ወረቀት ነው። ይህ የሚያያይዝ ትእዛዝ ባለ አደራውን (ገንዘብዎን፣ ሒሳብዎን ወይም ገቢዎን የያዘውን ሰው) ገንዘብዎን፣ ሒሳቦችዎን ወይም ገቢዎን ይዞ እንዲቆይና፣ እርስዎ እንዳይሰጥ ያዘዋል። ይህ ማለት፣ የእርስዎ ገንዘብ፣ ሒሳቦች ወይም ገቢ፣ በፍርድ ቤት ክስ ላይ እርስዎን ላሸነፈው ባለ እዳን ለመክፈል ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።

አንዳነድ ገንዘብ፣ ሒሳቦች ወይም ገቢ፣ የአደራ ስምምነት (ወይም የማያያዝ) ሒደት ተጠቅሞ ሊወሰዱ አይችሉም። ይህን የመሰለ ገንዘብ፣ ሒሳቦች ወይም ገቢ፣ ነጻ (ኤግዘምፐፕት) ተብሎ ይጠራል። **በዚህ ገጽ ጀርባ ላይ፣ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያና በፌደራል ሕግ መሰረት ባጠቃላዩ ነጻ የሆኑ ከፊላዊ ዝርዝር ይገኛል።** ነጻ እንዲደረግልዎ መብት አለኝ ብለው የሚያምኑ ከሆኑ፣ በክሱ ላይ ወዳሸነፈው (ወይም ጠበቃው፣ ካለዎት) በመደወል፣ ገንዘብዎ፣ ሒሳብዎ ወይም ገቢዎ ነጻ እንደሆነና፣ በፍርዱ ላይ ያሸነፈውን ግለሰብ (ወይም ጠበቃውን) ገንዘብዎን፣ ሒሳቦቹን፣ ወይም ገቢዎን እንዲለቅልዎ ይንገሩት።

**በፍርድቤትችሎትፊትየመቅረብመብትአልዎት።** ችሎት ፊት ለመቅረብ ለመጠየቅ፣ ነጻ እንዲደረግልዎ እና ችሎት ፊት ለመቅረብ መጠየቅያ (MotionforClaimofExemptionandRequestforHearing) አቤቱታ ማስገባት ይኖርብዎታል። የዚህ ማመልከቻ ናሙና ከጸሐፊ ቢሮ (አድራሻና የስልክ ቁጥር ከላይ ተጽፏል) ማግኘት ይቻላል። **ማመልከቻዎን *<u>በተቻልዎ መጠን ወዲያዉኑ</u>* ማስገባት ይኖርብዎታል። ቶሎ ብለው እርምጃ ካልወሰዱ፣ ያልዎትን ነጻ እንዲደረግልዎ የመጠየቅ መብትዎን ሊያጡና፣ ገንዘብዎ፣ ሒሳቦችዎ ወይም ገቢዎ፣ በፍርዱ ላይ ያሸነፈውን ለመክፈል አገልግሎት ላይ ሊውል ይችላል።**

ማመልከቻዎን በጸሐፊ ቢሮ ካስገቡ በኋላ፣ ከሚከተሉት በፊት ይደረግልኝ ብለው ጠይቀው እስካልሆነ ድረስ፣ አቤቱታውን ካስገቡበት ቀን ቢያንስ አስራ አንድ (11) የስራ ቀኖች ጠብቆ፣ ማመልከቻው በፖስታ ተልኮ ከሆነ ደግሞ ሶስት (3) የካሌንዳር ቀኖች ይጨመሩበትና፣ በችሎት ፊት እንዲቀርቡ ቀጠሮ ይያዝልዎታል። ነጻ እንዲደረግልዎ እና ችሎት ፊት ለመቅረብ መጠየቅያ አቤቱታ ሲያስገቡ፣ የፍርድ ቤቱ ጸሐፊ ችሎትዎ መቼ እንደሚሆን ይነግርዎታል።

ይህንን አቤቱታ ለማስገባት $10 መክፈል ይኖርብዎታል። ይህንን ገንዘብ መክፈል የማይችሉ ከሆኑ፣ ፍርድ ቤቱ ይህንን ገንዘብ ከመክፈል እንዲምርዎ መጠየቂያ ሌሎች ቅጾች መሙላት ይኖርብዎታል። እነዚህ ቅጾች "IFP"(ወይም*informapauperis*)ቅጾች ተብለው ይጠራሉ። ከፍርድ ቤቱ ጸሐፊ ቢሮ ደግሞ ሊያገኟቸው ይችላሉ።

**በችሎቱ ቀን ላይ፣ ገንዘብዎ፣ ሒሳቦችዎ ወይም ገቢዎ ለምን ነጻ መሆን እንዳለበት መግለጽ ይኖርብዎታል። ገንዘብዎ፣ ሒሳቦችዎ ወይም ገቢዎ ለምን ነጻ መሆን እንዳለበት እንደ ማስረጃ ሊያገለግልዎ የሚችሉ የሆኑ ሰነዶችን ይዘው መምጣት ይኖርብዎታል።** ለምሳሌ፣ ጥቅሞችዎ በባንክ ዲፖዚት መደረጋውቸን የሚያሳዩ የባንክ ስቴትመንቶችን ወይም ሌሎች እንደ ሶሻል ሰኩሪቲ ወይም የታክስ ሰነዶችን ማምጣት ይችላሉ።

**እነዚህን ደረጃዎች ካልተከተሉ፣ ወይም በችሎትዎ ላይ በፍርድ ቤቱ ካልተገኙ፣ የተወሰኑ መብቶችዎን ሊያጡ ይችላሉ። ከዚያ በኋላ፣ የተያዘው ገንዘብዎ፣ ሒሳቦችዎ ወይም ገቢዎ በፍርዱ ላይ ላሸነፈው ለመክፈል ሊያዝብዎ ይችላል።** ነጻ እንዲደረግልኝ መብት አለኝ የሚሉ ከሆኑ፣ ከጠበቃ ጋራ መነጋገሩ ጠቀሜታ ሊኖረው ይችላል። በዚህ ገጽ ጀርባ ላይ ከተጠቀሱት በነጻ ሕጋዊ አገልግሎቶችን ከሚሰጡ ኤጀንሲዎች አንዱ ጋራ መገናኘት ሊያስፈልግዎ ይችላል።

**ገንዘብዎ፣ ሒሳቦችዎ ወይም ገቢዎ አሸናፊውን ለመክፈል ሊወሰዱ ይችላሉ። ይህን ማስታወቅያ እባክዎን ተጠንቅቀው ያንብቡት።**

ከታች ነጻ የሆኑ የገንዘብ፣ ሒሳቦች ወይም የገቢ፣ ከፊላዊ የሆነ ሊስት ይገኛል። እነዚህ በጣም በማዘውተር ነጻ የሆኑት ብቻ ናቸው። እርስዎን የሚመለከቱ ሌሎች ተጨማሪ ነጻ የሆኑ ዝርዝሮች ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል። በመሆኑም፣ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ከጠበቃ ጋራ መነጋገር ሊኖርብዎ ይችላል።

እነዚህ ነጻነቶች፣ የትዳር አበል ወይም የልጅ ቀለብ/ድጋፍ ላይ ላይሰሩ ይችሉ እንደሆነ ይገንዘቡ። ለምሳሌ፣ የትዳር አበል ወይም የልጅ ቀለብ/ድጋፍን አስመልክቶ በእርስዎ ላይ የተበየነ ውሳኔ ካለ፣ ገንዘብዎ፣ ሒሳቦችዎ ወይም ገቢዎ ነጻ ነው ማለት አይችሉም ይሆናል። በሌላኛው ወገን፣ የትዳር አበል ወይም ድጋፍ እየተቀበሉ ከሆኑ፣ አብዛኛውን ግዜ ያ ገንዘብ ከየባለ አደራነት ወይም የማያያዝ ጥያቄ ነጻ ነው።

እባክዎን፣ ይህንን ገንዘብ፣ ሒሳቦችና ገቢ ነጻ የሚሆንባቸውን ዝርዝሮች ይመልከቱ። ነጻ እንዲደረግልዎ መብት አለኝ ብለው የሚያምኑ ከሆኑ፣ ችሎት ፊት ለመቅረብ አስመልክቶ በዚህ ወረቀት ላይ ባለው ፊተኛ ገጽ ላይ ያለውን መመሪያ ይከተሉ።

<u>ነጻ የሆኑከፊላዊ ዝርዝር</u>

- ሶሻል ሰኩሪቲ (SocialSecurity)(42U.S.C. § 407)
- ሳፐሊመንታል ሰኩሪቲ ገቢ (Supplemental Security Income)(SSI) (42 U.S.C. § 407)
- ሶሻል ሰኩሪቲ የስንክልና የመድን ዋስትና (SocialSecurityDisabilityInsurance)(SSDI)(42U.S.C. § 407)
- ለአባት ጦር የሚሰጡ ጥቅሞች (Veterans'Benefits)(38U.S.C. § 5301)
- የፌደራል ሰራተኞች የጡሮታ ጥቅሞች (FederalCivilServiceRetirementbenefits)(5U.S.C. § 8346)
- የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሰርቫይቨር ተቆራጮች (FederalCivilServiceSurvivorAnnuities)(5U.S.C. § 8346)
- ለአካለ ስንኩላን የሚሰጡ ጥቅሞች (Disabilitybenefits)(DCCode § 15-501(a)(7))
- የመንግስት ድጋፎች / የ TANFጥቅሞች(DCCode § 4-215)
- የስራ አጥነት ጥቅሞች (DCCode § 15-501(a)(7))
- በጡሮታ፣ የጡሮታ አበልና ተቆራጭ እቅዶች መሰረት የሚሰጡ ክፍያዎች*(DC Code § 15-501(a)(7))
- የትዳር አበል፣ ድጋፍ ወይም የተለየ ሜይንተናንስ*(DCCode§15-501(a)(7))
- የሰራተኛ ካሳ (DCCode § 32-1517)
- በሲቪላዊ ወይም የወንጀል ጉዳይ ላይ በፍርድ ቤት እንዲከፈሉ የተበየኑ ክፍያዎች*(DC Code § 15-501(a)(11))
- የባቡር መንገድ የጥሮታ መብት ጥቅሞች አዋጅ (Railroad Retirement Act benefits) (45 U.S.C. § 231m)
- ለሰርቫይቨርስ ኦፍ ፌደራል ጃጅስ የሚሰጡ ተቆራጮች (AnnuitiestoSurvivorsofFederal Judges) (28 U.S.C. § 376(n))
- የሎንግሾር ኤንድ ሃርበርዎርከርስ ኮምፐንሰሽኝ አዋጅ ጥቅሞች (LongshoreandHarborworkers'CompensationActBenefits)(33U.S.C. § 916)
- የሲማን ወይም ማስተርስ ወይም ፊሽርማን (Seaman'sorMaster'sorFisherman's) ደሞዞች(46U.S.C. § 1109)
- የጥቁር ሳምባ (BlackLung) ጥቅሞች(30U.S.C. § 932&33U.S.C. § 916)

***ውስንነቶችተግባራዊ ሊደረጉ ይችላሉ።**

ከጠበቃ ጋራ መነጋገር ከፈለጉ፣ የህግ አማካሪ ኤጀንሲ ሊስት በ www.lawhelp.org/dc ላይ ሊያገኙ ይችላሉ ወይም ደግሞ የሚከተሉትን የህግ ምክር አገልግሎት ቢሮዎች ጋር መገናኘት ይችላሉ። የሚቀበሉበትን የስራ ሰዓታት ለማወቅ እንዲችሉ፣ እያንዳንዱን ቢሮ በቀጥታ ማግኘት ይኖርብዎታል።

DCLawStudentsinCourt
806 7th Street NW, Suite 300Washington,DC
(202)638-4798

LegalCounselfor the Elderly
601E Street
NW,4th FloorWashington,DC20049
(202)434-2120

NeighborhoodLegalServices
701 4th Street
NWWashington,DC20001
(202)682-2700

Translated by JTG, Inc. 05/2017